

# Renting in Seattle

# አከራይ መሆን



ማከራየት ውስብስብ ሊሆን የሚችል ሲሆን ስለ ተከራይዎ መብቶች እና ግዴታዎች ማወቅ ያለብዎት ብዙ ነገር አለ። ይህ በራሪ ወረቀት ለጥገና ጥያቄ ስለማቅረብ፣ ተገቢ ስለሆነው መሰረተ ልማቶች፣ የቤት ዋጋን ለመጨመር፣ እና ሌሎች የማሳሰቢያ ዓይነቶች እና ከአከራይ ሊወስዷቸው ስለሚችሉት ነገሮችን የሚያሳይ መምሪያን ይሰጣል።

ይህን ድህረ ገጽ ይጎብኙ www.seattle.gov/rentinginseattle ወይም በሚከተለው ላይ በ Renting in Seattle Helpline (ስያትል ውስጥ ኪራይን ለማገዝ የሚረዳ መስመር) ላይ በ(206) 684-5700 ይደውሉ።

City of Seattle
Amharic




# የጥገና ጥያቄዎች

- ጥገና በሚያስፈልግበት ጊዜ ወዲያውኑ ለአከራይዎ በፍጥነት ያስታውቁ። አንዳንድ ጊዜ፣ ጥገና ማስፈለጉን አለመናገር ለሚፈጠረው ጥፋት እና ለጥገናው ወጪዎች ኃላፊነቱ እንዲወስዱ ሊደረጉ ይችላሉ። የሚያፈስ ቧንቧ ወይም የሚፈስ ሽንት ቤት ካለ የውኃ ክፍያ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ሊያመጣ ይችላል። ወዲያውኑ ካላሳወቁ የእርስዎ አከራይ እርስዎ ኃላፊነቱ እንደሚወስዱ ሊከራከርዎት ይችላል።
- የጥገና ጥያቄዎችን በጽሑፍ አድርገው ሊሰጡት ይገባዎታል። የእርስዎ አከራይ የጥገናውን በሕርይ መሰረት በማድረግ በተወሰነ የጊዜ ወሰን ውስጥ ምላሽ ሊሰጥዎት ይገባዋል።
- አከራይዎ ለጥገና ላቀረቡት ጥያቄ መልስ ለመስጠት ካልቻለ ወደ ስያትል Renting in Seattle Helpline ይደውሉ። መርማሪው ለምርመራ ቀጠሮ ይይዝ እና የእርስዎ አከራይ ማንኛውንም የሥነ ሥርዓት ደንብ ጥሰትን እንዲያርም ይጠይቃል።
- ከአከራይዎ ጋር አስቀድሞ በጽሑፍ የተቀመጠቀ ስምምነት ከሌለዎት በስተቀር ለጥገናው ተብሎ ኪራይን ወደኋላ ማስቀረት ወይም ከኪራይ ዋጋዎ ላይ የጥገና ወጪዎችን መቀነስ የመባረር አደጋ ላይ ሊያስቀምጥዎት ይችላል።



# የአከራይ መብት

- የእርስዎ አከራይ አስቀድሞ በማሳወቅ ለተወሰኑ ምክንያት የእርስዎን ክፍል መግባት መብት አለው።
  - የመሬት ባለቤቱ ለቀጣይ ተከራይ ወይም ገዢ ለማሳየት፣ ወይም በግምት በኮንትራት ለመስጠት በሚፈልግበት ጊዜ 1 **ቀን** በፊት ማሳወቅ አለበት።
  - አከራይ አስፈላጊውን ጥገና ወይም አስቀድሞ ስምምነት የተደረገበትን ማሻሻያን ለመስራት**2 ቀናት**
- አሳማኝ ምክንያት ካላችሁ ማለትም የቀጠሮ ግጭት ከተፈጠረ እንዳይገባ ሊከለክሉ ይችላሉ ነገር ግን አማራጭ ቀናት እና ጊዜያትን ማቅረባችሁን አረጋግጡ።
- ሕጉም ሁለታችሁንም ማለትም እርስዎን ወይም የእርስዎን አከራይ ክፍሉ ውስጥ ለመግባት አሳማኝ ምክንያት እንዲኖራችሁ ያዛል።
- ወደ ክፍሉ ለመግባት ከእርስዎ አከራይ ከመጣው ጥያቄ ጋር ለመተባበር ያደረጉትን ጥረት በሰነድ ያስቀምጡ። የእርስዎ አከራይ እንዳይገባ በመከለከል ከቀጠሉ፣ የ10-ቀናት ማሳሰቢያ በመስጠት እንዲገደዱ ወይም ባዶ እንዲያደርጉ ሊደረጉ ይችላሉ።
- የእርስዎ አከራይ ድንገተኛ ነገር በሚሆንበት ጊዜ፣ ማለትም እሳት ሲነሳ ወይም ከፍተኛ የሆነ ፍሳሽ በሚከሰትበት ጊዜ ለእርስዎ ሳያሳውቅ እና ስምምነትዎ ሳይኖር ወደ ክፍልዎ ሊገባ ይችላል።


# የቤት ዋጋን መጨመር



*የቤት ወጪ ኪራይን፣ የመኪና ማቆሚያ/የዕቃ ማስቀመጫ ክፍያዎችን ወይም ማንኛውም ከእርስዎ ቤት ጋር በመያያዝ የሚከሰቱ ወጪዎችን ያጠቃልላል።*

- በስያትል ውስጥ፣ የቤት ወጪ፣ 10% ወይም ከዚያ በላይ ለመጨመር አስቀድሞ ከ60 ቀናት በፊት በጽሑፍ ማሳሰቢያ መስጠትን ይጠይቃል። ከ10% በታች መጨመር ግን ከ30 ቀናት በፊት በጽሑፍ ማሳሰቢያ መስጠት ይጠይቃል።
- ማሳሰቢያዎቹም ስለ እርስዎ የማከራየት መብቶች እና የሁለቱንም ማለትም የከተማዋን እና የግዛቱን ደንቦች የሚጠይቁትን ያሟላል መሆኑን የሚገልጽ መረጃዎችን ማካተት አለባቸው።
- የእርስዎ የቤት ኪራይ በሚከተለው ድኅረገጽ ላይ ተዘርዝሮ የሚገኘውን መሰረታዊ መመዘኛ የማያሟላ ከሆነ *www.seattle.gov/rrio*፣ የእርስዎ አከራይ ጭማሬው ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት ችግሮቹን ማሟላት አለበት።
- የቤት ጭማሪው ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት ስለ ጉዳዩ ለእርስዎ አከራይ በጽሑፍ ማሳወቅ አለብዎት። ከተማዋ ጉዳዩን እና/ወይም ጥገናውን ለማረጋገጥ ምርመራ ያካሄዳል። ምርመራውን ቀጠሮ ለማስያዝ ወደ Renting in Seattle Helpline ይደውሉ።

# ሌሎች የተለመዱ ማሳሰቢያዎች




ከእርስዎ አከራይ ላይ ማሳሰቢያ በሚቀበሉበት ጊዜ ከፍተኛ ትኩረት ያድርጉበት። ከጊዜ አንጻር አስቸኳይ እና ደግሞም በጣም አስፈላጊ መረጃ ሊይዙ ይችላሉ። የእርስዎ አከራይ ማሳሰቢያውን በእጅዎ መስጠት ያለበት ሲሆን እርስዎ ካልተገኙ፣ በሚታይ ሁኔታ በቤትዎ በር ላይ መለጠፍ እና በመጀመሪያ ደረጃ ፓስታ ሳጥን በኩል ሊልክልዎት ይገባዋል።

- ***የኪራይ ስምምነት ላይ ለውጥ ለማድረግ ከ30 ቀናት በፊት ማሳሰብ:*** ከወር እስከ ወር በሚከራዩበት ጊዜ፣ የእርስዎ አከራይ ከ30 ቀናት በፊት በጽሑፍ ማሳሰቢያ በመስጠት የኪራይ ስምምነት ደንብ ላይ ለውጥ ሊያደርግ ይችላል። ማሰሰቢያውም ከኪራይ ጊዜ ፍጻሜ ጋር የተገጣጠመ መሆን አለበት።
- ***በ10 ቀናት ውስጥ መገደድ ወይም መልቀቅ:*** ይህ ማሳሰቢያ የሚሰራው የኪራይ ስምምነቱ ላይ ጥሰት ፈጽመው ከሆነ ነው። የታወቁት ምሳሌዎች ጸጥታ ማድረግ በሚገባ ሰዓት ላይ ጽምጽ ከፍ ማድረግ ወይም ማጨስ ባልተፈቀደው የሕንጻው ክፍል ውስጥ ማጨስን ሊያካትት ይችላል። ግዳጁን የማይቀበሉ ከሆነ፣ የመባረር አደጋ ላይ ሊሆኑ ይችላሉ። የማሳሰቢያውን እውነታዎች ላይ ከተከራከሩ፣ በጽሑፍ ምላሽ መስጠት አስፈላጊ ነው።
- ***በ 3 ቀናት ውስጥ መክፈል ወይም መልቀቅ:*** ይህ ማሳሰቢያ የሚሰራው ለዘገየ ኪራይ ክፍያ ነው። የኪራይ ክፍያዎን ማሳሰቢያው በደረስዎት በሦስት ቀናት ውስጥ መክፈል አለብዎ ወይም ለመባረር አደጋ ይዳረጋሉ። የኪራይ ክፍያዎን ዘግይተው እንደሚከፍሉ ካሰቡ፣ የእርስዎ አከራይ አስቀድሞ እንዲያውቀው ማድረጉ ጥሩ ነው። የእርስዎም አከራይ፣ በተለይም ደግሞ ሁሉ ጊዜ በጊዜ ይከፍሉ ከነበረ ጊዜ ሊሰጥዎት ይችላል(ከዚህ በታች ያለውን የኪራይ አጋዥ ቃል መግቢያውን ይመልከቱ)።
- ***የውል ማቋረጫ ማሳሰቢያ:*** ከእርስዎ አከራይ እንዲለቁ የሚያዝ ማሳሰቢያ ከተቀበሉ፣ ወደ ሚቀጥለው ድኅረገጽ ይሂድና ይዩ *www.seattle.gov/rentinginseattle* ወይም በስያትል (Seattle) ውስጥ የኪራይ ማስለቀቅ በራሪ ወረቀትን ይመልከቱ (ከዚህ በታች ያለውን የኪራይ አጋዥ ቃል መግቢያውን ይመልከቱ)።

ሰለ ተቀበሉት ማሳሰቢያ ለመረዳት እርዳታ ከፈለጉ ወይም ለሕጋዊ ምክር ለመላክ ከፈለጉ፣ ከ Renting in Seattle Helpline ጋር ግንኙነት ያድርጉ።

# የኪራይ ድጋፍ የቃል መግቢያዎች

ከኪራይ ጋር በተያያዘ ድጋፍ ለማግኘት ከፈለጉ ወደ ማኅበረሰብ የመረጃ መስመር ላይ በ211 ላይ ሊረዱዎት ወደሚችሉ ወደ ተዘረዘሩ ኤጄንሲዎች ጋር ይደውሉ።

በ3 ቀናት ውስጥ ኪራይ ስለመክፈል ወይም ስለመልቀቂ ማሳሰቢያ ከተቀበሉ እና የገንዘብ ድጋፍን ከሦስተኛ ወገን ካገኙ፣ የእርስዎ አከራይ በጽሑፍ የሆነ ክፍያ እንደሚፈጽሙ የሚገጽ ቃል መግብያ መቀበል አለበት። ሦስተኛው ወገን ቤተ ክርስቲያን፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ወይም ግለሰብ ሊሆን ይችላል።

- ቃል መግቢያውን በጽሑፍ መሆን አለበት።
- የ 3 ቀናቱ የማሳሰቢያ የጊዜ ገደብ ሳያልፍ መቀበል አለበት።
- ሦስተኛውም ወገን ለገባው ቃል ታማኝ በመሆን በአምስት ቀናት ውስጥ መክፈል አለበት።
- ክፍያውም በራሱ ወይም ከሌላ ገንዘብ ጋር በመቀላቀል እስከዚያ ቀን ድረስ ያለውን ለመሸፈን በቂ መሆን አለበት።






## የሚያሳምን መሰረተ ልማት እና ማሻሻያ

አካል ጉዳተኛ ሆነው እየተከራይ ከሆነ አሳማኝ የሆነ መሰረተ ልማት ወይም ማሻሻይን ሊጠይቁ ይችላሉ።

- የመሰረት ልማቱ በሕግ ወይም በተግባር ማለትም ልዩ ለሆነ ነገር መጠየቅ ማለትም የአካል ጉዳትዎ እንቅስቃሴዎ ላይ ተጽእኖ የሚያደርግ ከሆነ የመኪና ማቆሚያ ሕግን ለማሻሻል እንዲፈቀድልዎት እና መኪናውን ከመኖሪያ ቤትዎ አቅራቢያ እንዲያቆሙ የሚያደርገውን ማስለወጥ ነው።
- ማሻሻያ አካላዊ ለውጥ ማለትም ምቾትን የሚያሻሽለውን፣ ማለትም የመያዣ ደረጃ ወይም የዊልቸር ማስኬጃን ላይ የሚያደርግ ነው። የእርስዎ አከራይ የፌድራል የገንዘብ ድጋፍ ካላገኘ በስተቀር ወጪውን ለመሸፈን ኃላፊነቱ እርስዎ ይወስዳሉ።

## የአከራይ ከለላዎች

- እርስዎ መብትዎን ስለጠየቁ፣ ስለደረስብዎ ማግለል ቅሬታ ስላቀረቡ፣ ስለ ቤትዎ ወይም የእርስዎ አከራይ እርስዎን ለመበቀል ለእርስዎ አከራይ ሕጋዊ አይደለም። የቤት ኪራይን ለመጨመር፣ አገልግሎቶችን መቀነስ፣ ወይም እርስዎን ለማባረር መሞከር አንዳንድ የበቀል ምሳሌዎች ናቸው።
- አከራዮች ለማደራጀት ማለትም ስብሰባ ማዘጋጀት፣ በራሪ ወረቀትን ማሰራጨት ወይም የኪራይ ጉዳዮች ላይ ውይይት ለማድረግ ከሌሎች ተከራዮች ጋር ግንኙነት ለማድረግ መብት አላቸው።
- የእርስዎ አከራይ ቁልፎችን መለወጥ፣ የመጠቀሚያ ክፍሎችን መዝጋት፣ በሮችን/መኮቶችን፣ መሳሪያዎችን፣ ወይም ድልድሎችን ማስወስገድ ፈጽሞ የተከለከለ ነው።


**City of Seattle**

Seattle.gov/rentinginseattle

የዕርዳታ መስመር (206) 684-5700


ስያትል (Seattle) በአሳታፊነት እና በእኩልነት ታምናለች። ስደተኞች እና በመጠለያ ጣቢያ የሚኖሩ መምጣት ይችላሉ። የከተማ ሠራተኞች ስለ ዜግኔት ማንነት የማይጠይቅ ሲሆን የስደተኝነት ሁኔታ ላይ መሰረት ባለማድረግ ሁሉንም ነዋሪዎች ያገለግላል።

የአካል ጉዳት ካለብዎ እና በአማራጭ ፎርማት ከእኛ ላይ መረጃ ለመውሰድ ከፈለጉ፣ እባክዎን በኢጋዥ መስመር ላይ ይደውሉልን። የTTY መስመራችን (206) 233-7156 ነው።

**የትርጉም አገልግሎት ሁልጊዜ ይሰጣል። ይህ ሰነድ የሚገኝበት በ፡**

English • Español • Oromiffa • af Soomaali • አማርኛ • ភាសាខ្មែរ • 中文 • 한국어 • ພາສາລາວ
русский язык • ภาษาไทย • ትግርኛ • Tiếng Việt